መጽሐፈ ዕዝራ (Ezra)

ምዕራፍ 1።

1፤ በኤርምያስምአፍ የተናገረውየእግዚአብሔር ቃል ይፈጸምዘንድ በፋርስ ንጉሥበቂሮስ በመጀመሪያውዓመት እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥየቂሮስን መንፈስ አስነሣ፤ እርሱምበመንግሥቱ ሁሉ አዋጅ አስነገረ፥ ደግሞም በጽሕፈት አድርጎ እንዲህ አለ።

2፤ የፋርስ ንጉሥቂሮስ እንዲህ ይላል። የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን መንግሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል፤ በይሁዳምባለችውበኢያሩሳሌምቤት እሠራለት ዘንድ አዝዞኛል፤

3፤ ከሕዝቡ ሁሉ በእንናተ ዘንድ ማንምቢሆን አምላኩ ከእርሱ ጋር ይሁን፥ እርሱምበይሁዳ ወዳለችውወደ ኢያሩሳሌምይወጣ፥ በኢያሩሳሌምምለሚኖረውአምላክ፥ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ቤት ይሥራ፤

4፤ በሚኖርበትምስፍራ ሁሉ ለቀረውሰውየ አገሩ ሰዎች በብርና በወርቅ በዕቃምበእንስሳምይርዱት፤ ይህም በኢያሩሳሌምላለውለእግዚአብሔር ቤት በፈቃዳቸውከሚቀርቡት ሌላ ይሁን።

5፤ የይሁዳና የብንያምየ አባቶች ቤቶች አለቆችም፥ ካህናቱም፥ ሌዋውያኑም፥ በኢያሩሳሌምያለውን የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት ይወጡዘንድ እግዚአብሔር መንፈሳቸውን ያነ ሣሣውሁሉ ተነ ሡ።

6፤ በዙሪያቸውምያሉ ሁሉ በፈቃዳቸውካቀረቡት ሁሉ ሌላ በብር ዕቃና በወርቅ በገንዘቦችና በእንስሶች በሌላምስጦታ አገ ዙአቸው።

7፤ ንጉሥቂሮስምናቡከደነ ፆር ከኢያሩሳሌምወስዶ በአሞልክቱ ቤት ያኖራቸውን የእግዚአብሔርን ቤት ዕቃዎች አወጣ።

8፤ የፋርስ ንጉሥቂሮስምበመዝገ ቡላይ በነ በረውበሚትሪዳጡእጅ አወጣቸው፥ ለይሁዳምመኳንን ለሰሳብሳር ቈጠራቸው።

9፤ ቀጥራቸውምይህ ነ ው፤ ሠላሳ የወርቅ አንድ ሺህምየ ብር ሰሐኖች፥ ሀያ ዘጠኝምቢላዎች፥

10፤ ሠላሳ የወርቅ ደካዎች፥ አራት መቶ አሥርምሌላ ዓይነ ት የ ብር ደካዎች፥ አንድ ሺህምሌላ ዕቃ ነ በረ።

11፤ የወርቁና የ ብሩ ዕቃዎች ሁሉ አምስት ሺህ አራት መቶ ነ በሩ፤ እነ ዚህንምሁሉ ሰሳብሳር ከባቢሎን ወደ ኢያሩሳሌምከተማሉ ምርኮኞቹ ጋር ወሰደ።

ምዕራፍ 2።

1፤ የባቢሎንምንጉሥናቡከደነ ፆር ወደ ባቢሎን ከሚካቸውምርኮኞች ወደ ኢያሩሳሌምና ወደ ይሁዳ ወደ እየ ከተማቸውየ ተመላሱት የአገ ር ልጆች እነ ዚህ ናቸው።

2፤ ከዘሩባቤል፥ ከኢያሱ፥ ከነ ህምያ፥ ከሠራያ፥ ከረዕላያ፥ ከሞርዶክዮስ፥ ከበላሳን፥ ከሚሤር፥ ከበጉዋይ፥ ከሬሁም፥ ከበዓና ጋር ሞጡ።

3፤ የእስራኤልምሕዝብሰዎች ቍጥር ይህ ነ ው፤ የፋሮስ ልጆች፥ ሀለት ሺህ መቶ ሰባ ሀለት።

4፤ የሰፋጥያስ ልጆች፥ ሦስት መቶ ሰባ ሀለት።

5፤ የኤራ ልጆች፥ ሰባት መቶ ሰባ አምስት።

6፤ ከኢያሱና ከአዮአብ ልጆች የ ሆኑ የ ፈሐት ሞኣብ ልጆች፥ ሀለት ሺህ ስምንት መቶ አሥራ ሀለት።

7፤ የኤላምልጆች፥ ሺህ ሀለት መቶ አምሳ አራት።

8፤ የዛቱዕ ልጆች፥ ዘጠኝ መቶ አርባ አምስት።

9፤ የዘካይ ልጆች ሰባት መቶ ስድሳ።

10፤ የባኒ ልጆች፥ ስድስት መቶ አርባ ሀለት።

11፤ የቤባይ ልጆች፥ ስድስት መቶ ሀያ ሦስት።

12፤ የዓዝጋድ ልጆች፥ ሺህ ሀለት መቶ ሀያ ሀለት።

13፤ የአዶኒ ቃምልጆች፥ ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት።

14፤ የበጉዋይ ልጆች፥ ሀለት ሺህ አምሳ ስድስት።

15፤ የዓዲን ልጆች፥ አራት መቶ አምሳ አራት።

16፤ ከሕዝቅያስ ወገ ን የአጤር ልጆች፥ ዘጠና ስምንት።

17፤ የቤሳይ ልጆች፥ ሦስት መቶ ሀያ ሦስት።

18፤ የዮራ ልጆች፥ መቶ አሥራ ሀለት።

19፤ የሐሱምልጆች፥ ሀለት መቶ ሀያ ሦስት።

20፤ 21፤ የጋቤር ልጆች፥ ዘጠና አምስት። የቤተ ልሔምልጆች፥ መቶ ሀያ ሦስት።

22፤ የነ ጦፋ ሰዎች፥ አምሳ ስድስት።

23፤ የዓናቶት ሰዎች፥ መቶ ሀያ ስምንት።

24፤ የዓዝማት ልጆች፥ አርባ ሀለት።

25፤ የቂርያትይዓሪምና የከፊራ የብኤሮትምልጆች፥ ሰባት መቶ አርባ ሦስት።

26፤ የራሜ የጌባ ልጆች፥ ስድስት መቶ ሀያ አንድ።

27፤ የሜክሜስ ሰዎች፥ መቶ ሀያ ሁለት።

28፤ የቤቴልና የጋይ ሰዎች፥ ሁለት መቶ ሀያ ሦስት።

29፤ የናባውልጆች፥ አምሳ ሁለት።

30፤ የመጌብስ ልጆች፥ መቶ አምሳ ስድስት።

31፤ የሁለተኛውምኤላምልጆች፥ ሺህ ሁለት መቶ አምሳ አራት።

32፤ የካሪምልጆች፥ ሦስት መቶ ሀያ።

33፤ የሎድና የሐዲድ የኦኖምልጆች፥ ሰባት መቶ ሀያ አምስት።

34፤ የኢያሪኮ ልጆች፥ ሦስት መቶ አርባ አምስት።

35፤ የሴናዓ ልጆች፥ ሦስት ሺህ ስድስት መቶ ሠላሳ።

36፤ ካህናቱ፤ ከኢያሱ ወገን የዮዳኤ ልጆች፥ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሦስት።

37፤ የኢሜር ልጆች፥ ሺህ አምሳ ሁለት።

38፤ የፋስኮር ልጆች፥ ሺህ ሁለት መቶ አርባ ሰባት።

39፤ የካሪምልጆች፥ ሺህ አሥራ ሰባት።

40፤ ሌዋውያኑ፤ ከሆዳይዋ ወገን የኢያሱና የቀድምኤል ልጆች፥ ሰባ አራት።

41፤ ማዘምራኑ፤ የአሳፍ ልጆች፥ መቶ ሀያ ስምንት።

42፤ የበረኞች ልጆች፤ የሰሉምልጆች፥ የአጤር ልጆች፥ የጠልሞን ልጆች፥ የዓቁብ ልጆች፥ የሐጢጣልጆች፥ የሶባይ ልጆች፥ ሁሉ መቶ ሠላሳ ዘጠኝ።

43፤ ናታኒም፤ የሲሐ ልጆች፥ የሐሡፋ ልጆች፥

44፤ የጠበዖት ልጆች፥ የኬራስ ልጆች፥ የሲዓ ልጆች፤

45፤ የፋዶን ልጆች፥ የልባና ልጆች፥

46፤ የአጋባ ልጆች፥ የዓቁብ ልጆች፥ የአጋብ ልጆች፥ የሰምላይ ልጆች፥ የሐናን ልጆች፥

47፤ የጌደል ልጆች፥ የጋሐር ልጆች፥ የራያ ልጆች፥

48፤ የረአሶን ልጆች፥ የኔቆዳ ልጆች፥

49፤ የጋሴምልጆች፥ የዖዛ ልጆች፥ የፋሴሐ ልጆች፥

50፤ የቤሳይ ልጆች፥ የአስና ልጆች፥ የምዑናወያን ልጆች፥ የንፉሲሴምልጆች፥

51፤ የበቅበቅ ልጆች፥ የሐቁፋ ልጆች፥ የሐርሐር ልጆች፥

52፤ የበስለት ልጆች፥ የምሒዳ ልጆች፥

53፤ የሐርሳ ልጆች፥ የበርቆስ ልጆች፥

54፤ የሲሣራ ልጆች፥ የቴማልጆች፥ የንስያ ልጆች፥ የሐጠፋ ልጆች።

55፤ የሰሎሞንምባሪያዎች ልጆች፤ የሶጣይ ልጆች፥ የሶፈሬት ልጆች፥ የፍሩዳ ልጆች፥

56፤ የየዕላ ልጆች፥ የደርቆን ልጆች፥ የጌዴል ልጆች፥

57፤ የሰፋጥያስ ልጆች፥ የሐጠል ልጆች፥ የፈከራት ልጆች፥ የሐጺቦይምልጆች፥ የአሚልጆች።

58፤ እነዚህ ናታኒምሁሉና የሰሎሞን ባሪያዎች ልጆች ሦስት መቶ ዘጠና ሁለት ነበሩ።

59፤ ከቴልሜል፥ ከቴላሬሳ፥ ከከሩብ፥ ከአዳን፥ ከኢሜር የወጡእነዚህ ነበሩ፤ ነገር ግን የአባቶቻቸውን ቤቶችና ዘራቸውን ወይምከእስራኤል ወገን መሆናቸውን ያስታወቁ ዘንድ አልቻሉም፤

60፤ የዳላያ ልጆች፥ የጦቢያ ልጆች፥ የኔቆዳ ልጆች፥ ስድስት መቶ አምሳ ሁለት ነበሩ።

61፤ ከካህናቱምልጆች፤ የኤብያ ልጆች፥ የአቆስ ልጆች፥ ከገለዓዳዊውከቤርዜሊ ልጆች ሚስት ያገባ፥ በስመም የተጠራ የቤርዜሊ ልጆች።

62፤ እነዚህ በትውልድ መጽሐፍ ትውልዳቸውን ፈለጉ፤ ነገር ግን አልተገኘም፥ ከክህነ ትምተከለከሉ።

63፤ ሐቴርሰታም፡ በኡሪምና በቱሚምየ ሚፈርድ ካህን እስኪነሣ ድረስ ከቅዳሰ ቅዳሳን አትበሉምአላቸው።

64፤ 65፤ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሠላሳ ሰባት ከነበሩ ከሰሌዎቻቸውና ከገረዶቻቸውሌላ ጉባኤውሁሉ አርባ ሁለት ሺህ ሦስት መቶ ስድሳ ነበሩ። ሁለት መቶምወንዶችና ሴቶች መዘምራን ነበሩአቸው።

66፤ ፈረሶቻቸውምሰባት መቶ ሠላሳ ስድስት በቅሎቻቸውምሁለት መቶ አርባ አምስት፥

67፤ ግመሎቻቸውምአራት መቶ ሠላሳ አምስት፥ አህዮቻቸውምስድስት ሺህ ሰባት መቶ ሀያ ነበሩ።

68፤ በኢያሩሳሌምምወዳለውወደ እግዚአብሔር ቤት በመጡጊዜ ከአባቶች ቤቶች አለቆች አያሌዎች ለእግዚአብሔር ቤት በስፍራውይሠራ ዘንድ በፈቃዳቸውሰጡ።

69፤ ስድሳ አንድ ሺህምየ ወርቅ ዳሪክ፥ አምሳት ሺህምሚን ብር፥ አንድ መቶምየ ካህናት ልብስ እንደ ችሎታቸውወደ ሥራውቤተ መዛግብት አቀረቡ።

70፤ ካህናቱና ሌዋውያኑም፥ ከሕዝቡምአያሌዎች፥ መዘምራኑና በረኞቹም፥ ናታኒምምበከተሞቻቸው፥ እስራኤልምሁሉ በከተሞቻቸውተቀመጡ።

ምዕራፍ 3።

1፤ ሰባተኛውምወር በደረሰ ጊዜ፥ የእስራኤልምልጆች በከተሞቻቸውሳሉ፥ ሕዝቡእንደ አንድ ሰውሆነ ውወደ ኢያሩሳሌምተሰበሰቡ።

2፤ የኢዮሴዴቅምልጅ ኢያሱ፥ ወንድሞቹምካህናቱ፥ የሰላትያልምልጅ ዘሩባቤል ወንድሞቹምተነ ሥተው በእግዚአብሔር ሰውበሚሴ ሕግ እንደ ተጻፈ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ያቀርቡበት ዘንድ የእስራኤልን አምላክ መሠዊያ ሠሩ።

3፤ በአገሩምካሉት አሕዛብ ፈርተውነ በርና መሠዊያውን በስፍራውላይ አስቀመጡት፥ በጥዋትና በሜዛም የሚቃጠለውን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረቡት።

4፤ እንደ ተጻፈውምየ ዳስ በዓል አደረጉ፤ እንደ ሥርዓቱምለየ ዕለቱ የተገባውን የየ ዕለቱን የሚቃጠል መሥዋዕት በቁጥር አቀረቡ።

5፤ ከዚያምበኋላ ዘወትር የሚቃጠለውን መሥዋዕት፥ የመባቻውንምመሥዋዕት፥ የተቀደሱትንምየእግዚአብሔር በዓላት ሁሉ መሥዋዕት፥ ሰወምሁሉ ለእግዚአብሔር በፈቃድየ ሰጡትን ቀርባን አቀረቡ።

6፤ በሰባተኛውወር በመጀመሪያውቀን ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ማቅረብ ጀመሩ፤ የእግዚአብሔር መቅደስ ገና አልተመሠረተምነ በር።

7፤ ለጠራቢዎችና ለአናጢዎችምገንዘብሰጡ፤ የፋርስምንጉሥቂሮስ እንደ ፈቀደላቸውየ ዝግባ ዛፍ ከሊባኖስ በባሕር ወደ ኢዮጴ ያጫዝንድ ለሲዶናና ለጢሮስ ሰዎች መባልና ማጠጥ ዘይትምሰጡ።

8፤ በኢያሩሳሌምወዳለውወደ እግዚአብሔር ቤት በጫበሀለተኛውዓመት በሀለተኛውወር የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤል፥ የኢዮሴዴቅምልጅ ኢያሱ፥ የቀሩትምወንድሞቻቸውካህናትና ሌዋውያን፥ ወደ ኢያሩሳሌምም የተመለሱት ምርኮኞች ሁሉ ጀመሩ፤ ሌዋውያንንምከሀያ ዓመት ጀምሮ ከዚያምበላይ የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ እንዲያሠሩት ሾመላቸው።

9፤ ኢያሱምልጆቹምወንድሞቹም፥ የይሁዳምልጆች ቀድምኤልና ልጆቹ፥ የኤንሐዳድምልጆች፥ ልጆቻቸውና ወንድሞቻቸውሌዋውያንምየ እግዚአብሔርን ቤት የሚሥሩትን ያሠሩ ዘንድ በአንድነት ቆሙ።

10፤ አናጢዎቹምየእግዚአብሔርን መቅደስ በመሠረቱ ጊዜ ካህናቱ ልብሳቸውን ለብሰውመለከቱን ይዘው፥ የአሳፍምልጆች ሌዋውያን ጸናጽል ይዘውእንደ እስራኤል ንጉሥእንደ ዳዊት ሥርዓት እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ዘንድ ቆሙ።

11፤ ደግሞ፡ ቸር ነውና፥ ለእስራኤልምምሕረቱ ለዘላለምነውና እያሉ እግዚአብሔርንምእያመሰገኑና እያከበሩ እርስ በእርሳቸውያስተዛዝሉ ነበር፤ የእግዚአብሔርምቤት ስለ ተመሠረተ ሕዝቡ ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በታላቅ ደምፅ እልል አሉ።

12፤ የፊተኛውን ቤት ያዩ ሽማግሌዎች የሆኑ ብዙ ካህናትና ሌዋውያን የአባቶችምቤቶች አለቆች ግን ይህ መቅደስ በፊታቸውበተመሠረተ ጊዜ በታላቅ ድምፅ ያለቅሱ ነበር፤ ብዙ ሰዎችምበደስታ ይጮኹ ነበር፤

13፤ ደስ ብለአቸውየ ሚጮኹትን ድምፅ ከሕዝቡ ልቅሶ ድምፅ መለየ ት የ ሚቻል አልነ በረም፤ ሕዝቡምበታላቅ ድምፅ ይጮኽ ነበር፥ ድምፁምከሩቅ ይሰማነ በር።

ምዕራፍ 4።

1፤ የይሁዳና የብንያምመለቶች ምርኮኞቹ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር መቅደስ እንደ ሠሩ ሰሙ፥

2፤ ወደ ዘሩባቤልና ወደ አባቶች ቤቶች አለቆች ቀርበው። የአሦር ንጉሥአስራዶን ወደዚህ ካመጣን ቀን ጀምሮ ለአምላካችሁእንሠዋለንና፥ እንደ እናንተምእንፈልገ ዋለንና ከእናንተ ጋር እንሥራ አሉአቸው።

3፤ ዘሩባቤልና ኢያሱምየ ቀሩትምየ እስራኤል አባቶች ቤቶች አለቆች። የ አምላካችንን ቤት መሥራት ለእኛና ለእናንተ አይደለም፤ እኛ ለብቻችን ግን የ ፋርስ ንጉሥቂሮስ እንዳዘዘን ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ቤት እንሠራለን አሉአቸው።

4፤ የ ምድሩምሕዝብ የ ይሁዳን ሕዝብ እጅ ያደክሙኅ በር፥ እንዳይሠሩምአስፈራሩአቸው፥

5፤ ምክራቸውንምያፈርሱ ዘንድ በፋርሱ ንጉሥበቂሮስ ዘመን ሁሉ እስከ ፋርስ ንጉሥእስከ ዳርዮስ መንግሥት ድረስ መካሪዎችን ገዙባቸው።

6፤ በአርጤክስስምመንግሥት፥ በመንግሥቱምበመጀመሪያ ዘመን፥ በይሁዳና በኢያሩሳሌምበሚኖሩት ላይ የ ክስ ነገር ጻፉ።

7፤ በአርጤክስስ ዘመን ቢሽላም፥ ሚትሪዳጡ፥ ጣብኤል ተባባሪዎቹምለፋርስ ንጉሥለአርጤክስስ ጻፉ፤ ደብዳቤውምበሶርያ ፊደልና በሶርያ ቋንቋ ተጽፎ ነበር።

8፤ አዛዡሬሀምጸሐፊውምሲምሳይ በኢያሩሳሌምላይ ለንጉሡለአርጤክስስ እንዲህ የ ሚል ደብዳቤ ጻፉ።

9፤ አዛዡሬሀምጸሐፊውምሲምሳይ የ ቀሩትምተባባሪዎቻቸው፥ ዲናውያን፥ አፈርሳትካውያን፥ ጠርፈላውያን፥ አፈርሳውያን፥ አርካውያን፥ ባቢሎናውያን፥ ሱሳናካውያን፥ ዴሐውያን፥ ኤላማውያን፥

10፤ ታላቁና ኃይለኛውአስናፈር ያፈለሳቸውበሰማርያና በወንዝ ማዶ ያኖራቸውየ ቀሩትምአሕዛብ ደብዳቤውን ጻፉ።

11፤ ለንጉሡለአርጤክስስ የ ላኩት የ ደብዳቤ ግልባጭይህ ነው። በወንዝ ማዶ ያሉት ሰዎች ባሪያዎችህ፤

12፤ አሁንምከአንተ ዘንድ የ ወጡአይሁድ ወደ እኛ ወደ ኢያሩሳሌምእንደ ሚኩንጉሡይወቅ፤ ዓመፀኛይቱንና እጅግምየ ከፋቺቱን ከተማይሠራሉ፥ ቅጥርዋንምያድሳሉ፥ መሠረትዋንምጠ ኑ።

13፤ አሁንምይህች ከተማየ ተሠራች እንደ ሆነ ፥ ቅጥርዋምየ ታደሰ እንደ ሆነ ፥ ግብርና ቀረጥ መንገም እንዳይሰጡ፥ የ ንጉሥምግቢውእንዲጉድል ንጉሥይወቅ።

14፤ የንጉሣምጪውእንበላለንና፥ ንጉሣምሲያቃልሉት ሟ ት አይገ ባንምና ስለዚህ ልከን ለንጉሡ አስታወቀናል፤

15፤ በአባቶችህ ታሪክ መጽሐፍ ምርመራ ይደረግ፤ በዚያምበታሪክ መጽሐፍ ይህች ከተማዓመፀኛ እንደ ሆነ ች፥ ነ ገ ሥታትንና አወራጃዎችንምእንደ ጐዳች፥ ከጥንቱምሽፍትነ ት በእርስዋ እንደ ተጀመረ ታገ ኛለህ፥ ታውቃለህም፤ ስለዚህምይህች ከተማፈርሳ ነ በር።

16፤ ይህችምከተማየ ተሠራች እንደ ሆነ ፥ ቅጥርዋምየ ታደሰ እንደ ሆነ ፥ በወንዝ ሜዶ ክፍል እንደሌለህ ለንጉሡእናስታወቃለን።

17፤ ንጉሣምለአዛዡለሬሀም፥ ለጸሐፊወምለሲምሳይ፥ በሰሜርያና በወንዝ ሜዶምለተቀማጡለቀሩት ተባባሪዎቻቸውእንዲህ የሚለዉን መልስ ላከ።

18፤ ሰላም፤ አሁንምወደ እኛ የላካችሁት ደብዳቤ በፊቴ ተተርጕሞተነ በበ።

19፤ እኔ ምአዝኅሉሁ፥ ተመረመረም፤ ይህችምከተማከጥንት ጀምራ በነ ገ ሥታት ላይ ዓመፀኛ እንደ ነ በረች፥ በእርስዋምዓመፅ ና ሽፍትነ ት እንደ ተደረገ ተገ ኘ።

20፤ በኢያ ሩሳሌምምእጅግ ኃያላን ነ ገ ሥታት ነ በሩ፥ በወንዝምሜዶ ያለዉን አገ ር ሁሉ ይገ ዙ ነ በር፤ ግብርንና ቀረጥን መጮንንምይቀበሉ ነ በር።

21፤ አሁንምእነ ዚህ ሰዎች ሥራውን እንዲተው፥ እኔ ምእስካዝዝ ድረስ ይህች ከተማእንዳትሠራ ትእዛዝ ስጡ።

22፤ ቸልምእንዳትሉ ተጠንቀቁ፤ ለነ ገ ሥታቱ ጉዳትና ጥፋት እየ በዛ ስለ ምን ይሄዳል?

23፤ የንጉሣምየ አርጤክስስ ደብዳቤ ግልባጭብሬሀምና በጸሐፊውበሲምሳይ በተባባሪዎቻቸውምፊት በተነ በበ ጊዜ ፈጥነ ውወደ ኢያ ሩሳሌምወደ አይሁድ ሄዱ፤ በግድና በኃይልምአስተወአቸው።

24፤ በዚያን ጊዜምበኢያ ሩሳሌምያለውየ እግዚአብሔር ቤት ሥራ ቀረ፤ እስከ ፋርስምንጉሥእስከ ዳርዮስ መንግሥት እስከ ሁለተኛውዓመት ድረስ ተጓጉለ።

ምዕ ራፍ 5።

1፤ ነ ቢያቱምሐጌና የአዶ ልጅ ዘካርያስ በይሁዳና በኢያ ሩሳሌምለነ በሩ አይሁድ በእስራኤል አምላክ ስም ትንቢት ተናገ ሩላቸው።

2፤ በዚያን ጊዜ የሰላትያል ልጅ ዘሩባቤል የኢዮሴዴቅምልጅ ኢያሱ ተነ ሥተውበኢያ ሩሳሌምያለዉን የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት ጀመሩ፤ የሚያግዙአቸውምየ እግዚአብሔር ነ ቢያት ከእነ ርሱ ጋር ነ በሩ።

3፤ በዚያምዘመን በወንዝ ሜዶ የነ በረውገ ዥተንትናይ፥ ደግሞሰተርበዝናይ፥ ተባባሪዎቻቸውምወደ እነ ርሱ መጥተው። ይህን ቤት ትሠሩ ዘንድ፥ ይህንኑምቅጥር ታድሱ ዘንድ ያዘዛችሁ ማን ነ ዉ? አሉአቸው።

4፤ ደግሞም፥ ይህንስ ሥራ የሚሠሩት ሰዎች ስምማን ነ ዉ? ብለውጠየ ቁአቸው።

5፤ የአምላካቸውዓይን ግን በአይሁድ ሽማግሌዎች ላይ ነበረ፥ ይህምነገር ወደ ዳርዮስ እስኪደርስ ድረስ፥ መልሰም በደብዳቤ እስኪመጣድረስ አልከለከሉአቸውም።

6፤ በወንዙ ማዶ የነበረውገዥተንትናይ ደግሞሰተርቡዝናይ ተባባሪዎቹምበወንዙ ማዶ የነበሩት አፈርስካውያን ወደ ንጉሡወደ ዳርዮስ የላኩት የደብዳቤውግልባጭይህ ነበረ።

7፤ እንዲህምየሚል ደብዳቤ ላኩለት። ለንጉሥለዳርዮስ ሙሉ ሰላምይሁን፤

8፤ ወደ ይሁዳ አገር ወደ ታላቁምአምላክ ቤት እንደ ሄድን ንጉሥይወቅ፤ እርሱምበትልቅ ድንጋይ ተሠራ፥ በቅጥሩምወስጥ እንጨት ተደረገ፥ ያምሥራ በትጋት ይሠራል፥ በእጃቸውምይከናወናል።

9፤ እነዚያንምሽማግሌዎች። ይህን ቤት ትሠሩ ዘንድ፥ ይህንስ ቅጥር ታድሱ ዘንድ ያዘዛችሁማን ነው? ብለን ጠየቅናቸው።

10፤ ደግሞምእናስታወቅህ ዘንድ፥ በእነርሱምያሉትን ሹማቸው ስምእንጽፍልህ ዘንድ ስማቸውን ጠየቅን።

11፤ እንደዚህምብለውመለሱልን። እኛ የሰማይና የምድር አምላክ ባሪያዎች ነን፥ ከብዙምዘመን ጀምሮ ተሠርቶ የነበረውን፥ ታላቁምየእስራኤል ንጉሥሠርቶ የፈጸመውን ቤት እንሠራለን።

12፤ አባቶቻችንምየሰማይን አምላክ ካስቈጠብኋላ በከለዳዊውበባቢሎን ንጉሥበናቡከደነፆር እጅአሳልፎ ሰጣቸው፥ እርሱምይህን ቤት አፈረሰ፥ ሕዝቡንምወደ ባቢሎን አፈለሰ።

13፤ ነገር ግን በባቢሎን ንጉሥበቂሮስ በመጀመሪያውዓመት ንጉሡቂሮስ ይህን የእግዚአብሔርን ቤት ይሠሩ ዘንድአዘዘ።

14፤ ናቡከደነፆርምበኢያሩሳሌምከነበረውመቅደስ የወሰደውን፥ ወደ ባቢሎንምመቅደስ ያፈለሰውን የእግዚአብሔርን ቤት የወርቅንና የብርን ዕቃንጉሡቂሮስ ከባቢሎን መቅደስ አወጣቶ ሰሳብሳር ለተባለው ለሾመሰጠውና።

15፤ ይህን ዕቃይዘህ ሂድ፥ በኢያሩሳሌምምባለውመቅደስ አኑረው፤ የእግዚአብሔርምቤት በስፍራውይሠራ አለው።

16፤ በዚያ ጊዜምይህ ሰሳብሳር መጣ፥ በኢያሩሳሌምምያለውን የእግዚአብሔርን ቤት መሠረተ፤ ከዚያምጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እየተሠራ አልተጨረሰም።

17፤ አሁንምይህ ነገር በንጉሡላይን መልካምቢሆን ይህ የእግዚአብሔር ቤት በኢያሩሳሌምይሠራ ዘንድ ከንጉሡከቂሮስ ታዝዞ እንደ ሆነ በባቢሎን ባለውበንጉሡቤተ መዛግብት ይመርመር፤ ስለዚህምነገር ንጉሡ ፈቃዱን ይላክልን።

ምዕራፍ 6።

1፤ በዚያ ጊዜምንጉሡዳርዮስ መዛግብት ባሉበት በባቢሎን ቤተ መጻሕፍት እንዲመረመር አዘዘ።

2፤ በሜዶን አወራጃ ባለውአክምታ በሚገል ከተማበንጉሡቤት ወስጥ አንድ ጥቅልል ተገኘ፥ በወስጡምይህ ነገር ለመታሰቢያ ተጽፎ ነበር።

3፤ በንጉሥበቂሮስ በመጀመሪያውዓመት ንጉሥቂሮስ እንዲህ ብሎአዘዘ፤ በኢያሩሳሌምያለውየእግዚአብሔር ቤት፥ መሥዋዕት የሚቀርብበት ቦታ፥ ይህ ቤት ይሠራ፥ በጽኑምይመሠረት፤ ቁመቱ ስድሳ ክንድ ወርዱምስድሳ ክንድ ይሁን።

4፤ በሦስት ተራ ታላላቅ ድንጋይ፥ በአንድ ተራ እንጨት ይደረግ፤ ወጪውምከንጉሡቤት ይሰጥ።

5፤ ናቡከደነፆርምበኢያሩሳሌምካለውመቅደስ ወስዶ ወደ ባቢሎን ያመጣውየእግዚአብሔር ቤት የወርቅና የብር ዕቃ ይመለስ፤ በኢያሩሳሌምም ወዳለውመቅደስ ወደ ስፍራውይወሰድ፥ በእግዚአብሔር ቤት ይኑር።

6፤ አሁንምአንተ በወንዝ ማዶ ያለኸውየአገሩ ገዥተንትናይ ደግሞሰተርቡዝናይ በወንዝ ማዶምያሉ ተባባሪዎቻችሁአፈርስካወያን፥ ከዚያ ራቁ፤

7፤ ይህምየእግዚአብሔር ቤት ይሠራ ዘንድ ተወ፤ የአይሁድምአለቃና የአይሁድምሽማግሌዎች ይህን የእግዚአብሔርን ቤት በስፍራውይሠሩ ዘንድ ተወኣቸው።

8፤ ይህን የእግዚአብሔርን ቤት ይሠሩ ዘንድ ለአይሁድ ሽማግሌዎች የምታደርጉትን፥ በወንዝ ማዶ ካለውአገር ከሚመጣውግብር ከንጉሥገንዘብ ለእነ ዚህ ሰዎች ወጪዎን በትጋት እንድትሰጠኣቸውሥራምእንዳታስፈቱአቸው አዝዣለሁ።

9፤ ለሰማይ አምላክ ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆንፈልገውን፥ ወይፈኖችና አውራ በጎች ጠቦቶችም፥ በኢያሩሳሌምምእንዳሉ እንደ ካህናቱ ቃል ስንዴና ጨውየ ወይን ጠጅና ዘይት ዕለት ዕለት ያለሚቋረጥ ስጠኣቸው።

10፤ ይኸውምለሰማይ አምላክ ጣፋጭሽቱ የሆነ ወን መሥዋዕት ያቀረቡ ዘንድ ለንጉሡና ለልጆቹምዕድሜይጸልዩ ዘንድነ ው።

11፤ ይህንምትእዛዝ የሚላወጥ ሁሉ፥ ምሰሶውከቤቱ ተነ ቅሎእርሱ ይሰቀልበት፤ ቤቱምየ ጉድፍ መጣያ ይደረግ ብዬ አዝዣለሁ።

12፤ ስማንምበዚያ ያኖረውአምላክ ይህን ይለወጠዘንድ በኢያሩሳሌምያለወንምየእግዚአብሔርን ቤት ያፈርሱት ዘንድእጃቸወን የሚዘረጉትን ነገሥትና አሕዛብ ሁሉ ያጥፋ። እኔ ዳርዮስ ይህን አዝዣለሁ፤ በትጋት ይፈጸሙ።

13፤ ንጉሡምዳርዮስ እንደ ላከውቃል፥ በዚያን ጊዜ በወንዝ ማዶ ያለ ገዥተንትናይ ደግሞሰተርቡዝናይ ተባባሪዎቻቸውምእንዲሁ ተግተውአደረጉ።

14፤ የአይሁድምሽማግሌዎች በነቢዩ በሐጌና በአዶ ልጅ በዘካርያስ ትንቢት ሠሩ ተከናወነ ላቸወም። እንደ እስራኤልምአምላክ ትእዛዝ፥ እንደ ፋርስምነገሥት እንደ ቂሮስና እንደ ዳርዮስ እንደ አርጤክስስም ትእዛዝ ሠርተውፈጸሙ።

15፤ ይህምቤት በንጉሡበዳርዮስ መንግሥት በስድስተኛውዓመት አዳር በሚል ወር በሦስተኛውቀን ተፈጸመ።

16፤ የእስራኤልምልጆች፥ ካህናትና ሌዋውያን የቀሩትምምርኮኞች፥ የዚህን የእግዚአብሔርን ቤት ቅዳሴ በደስታ አደረጉ።

17፤ በዚህምበእግዚአብሔር ቤት ቅዳሴ መጾ ወይፈኖችና ሀለት መጾ አወራ በጎች አራት መጾምጠቦቶች አቀረቡ ፤ ስለ ኃጢአትምመሥዋዕት እንደ እስራኤል ነገዶች ቁጥር ለእስራኤል ሁሉ አሥራ ሀለት አወራ ፍየሎች አቀረቡ።

18፤ በሚኤምመጽሐፍ እንደ ተጻፈውበኢያሩሳሌምባለውበእግዚአብሔር አገልግሎት ላይ ካህናቱን በየ ማዕርጋቸውሌዋዉያኑምበየ ክፍላቸውአቆሙ።

19፤ ምርኮኞቹምበመጀመሪያውወር በአሥራ አራተኛውቀን ፋሲካወን አደረጉ።

20፤ ካህናቱና ሌዋዉያኑምአንድ ሆነ ውነ ጽተውነ በር ፤ ሁሉምንጹሐን ነበሩ፤ ለምርኮኞቹምሁሉ፥ ለወንድሞቻቸውምለካህናቱ፥ ለራሳቸውምፋሲካወን አረዱ።

21፤ ከምርኮምተመልሰውየ ማከት የእስራኤል ልጆች፥ የእስራኤልንምአምላክ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ ራሳቸውን ከምድር አሕዘብርከሰት ለይተውወደ እነ ርሱ መጥተውየ ነበሩት ሁሉ በሉ፤

22፤ እግዚአብሔር ደስ አሰኝቶአቸዋልና ፥ የእስራኤልንምአምላክ የእግዚአብሔርን ቤት ለመሥራት እጃቸውን ያጸና ዘንድየአሦርን ንጉሥልብ ወደ እነ ርሱ መልሶአልና የቂጣውን በዓል ሰባት ቀን በደስታ አደረጉ።

ምዕራፍ 7።

1፤ ከዚህምነገር በኋላ በፋርስ ንጉሥበአርጤክስስ መንግሥት ዕዝራ የሠራያ ልጅ፥

2፤ የዓዛርያስ ልጅ፥ የኬልቅያስ ልጅ፥ የሰሉምልጅ፥ የሳዶቅ ልጅ፥ የአኪጡብ ልጅ፥

3፤ የአሚርያ ልጅ፥ የዓዛርያስ ልጅ፥ የሜራዮት ልጅ፥

4፤ የዘራእያ ልጅ፥ የኦዚ ልጅ፥ የቡቂ ልጅ፥

5፤ የአቢሱ ልጅ፥ የፊንሐስ ልጅ፥ የአልዓዛር ልጅ፥ የታላቁ ካህን የአሮን ልጅ፥ ይህ ዕዝራ ከባቢሎን ወጣ፤

6፤ የእስራኤልምአምላክ እግዚአብሔር በሰጠውበሚኬሕግ ፈጣን ጸሐፌ ነበረ ፤ የአምላክምየእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ነበረችና ንጉሡየሻወን ሁሉ ሰጠው።

7፤ ከእስራኤልምልጆች ከካህናቱምከሌዋዉያኑምከመዘምራኑምከበረኞቹምከናታኒ ምምበንጉሡበአርጤክስስ በሰባተኛውዓመት አያሌዎች ወደ ኢያሩሳሌምወጡ።

8፤ በንጉሡምበሰባተኛውዓመት በአምስተኛውወር ወደ ኢያሩሳሌምደረሰ።

9፤ በመጀመሪያወምወር በአንደኛውቀን ከባቢሎን ሊወጣጀመረ ፥ መልካሚዙምየአምላኩእጅ በእርሱ ላይ ነበረችና በአምስተኛ ወር በመጀመሪያውቀን ወደ ኢያሩሳሌምደረሰ።

10፤ ዕዝራምየእግዚአብሔርን ሕግ ይፈልግና ያደርግ ዘንድ፥ ለእስራኤልምሥርዓትንና ፍርድን ያስተምር ዘንድ ልቡን አዘጋጅቶ ነበር።

11፤ ንጉሡምአርጤክስስ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቃልና ለእስራኤል የሆነ ውን ሥርዓት ይጽፍ ለነበረው ለጸሐፊውለካህኑ ለዕዝራ የሰጠውየደብዳቤውግልባጭይህ ነው።

12፤ ከንጉሥ ነገሥት ከአርጤክስስ ለሰማይ አምላክ ሕግ ጸሐፊ ለካህኑ ለዕዝራ፥ ሙሉ ሰላምይሁን፤

13፤ በመንግሥቴ ወስጥ ካሉ ከእስራኤል ሕዝብ ከካህናቱና ከሌዋውያኑምወደ ኢያሩሳሌምይሄድ ዘንድ የሚወድድ ሁሉ ከአንተ ጋር እንዲሄድ አዝንሊሁ።

14፤ በእጅህ እንዳለችውእንደ አምላክህ ሕግ ይሁዳንና ኢያሩሳሌምን ትገብኝ ዘንድ፥

15፤ ንጉሣንና አማካሪዎቹምመኖሪያውበኢያሩሳሌምለሆነ ውለእስራኤል አምላክ በፈቃዳቸውያቀረቡትን ብርና ወርቅ፥

16፤ በባቢሎንምአውራጃ ሁሉ የምታገኘውን ብርና ወርቅ ሁሉ፥ ሕዝቡና ካህናቱምበኢያሩሳሌምላለው ለአምላካቸውቤት በፈቃዳቸውየ ሚቀርቡትን ትወስድ ዘንድ በንጉሥና በሰባቱ አማካሪዎች ተልከሃልና፤

17፤ ስለዚህ በዚህ ገንዘብ ወደፈኖችንና አወራ በጎችን ጠቦቶችንምየ እህላቸውንና የ መጠጡውን ቀርባን ተግተህ ግዛ፤ በኢያሩሳሌምምባለውበአምላካችሁ ቤት መሠዊያ ላይ አቅርባቸው።

18፤ ከቀረወምብርና ወርቅ አንተና ወንድሞችህ ለማድረግ ደስ የሚሰኛችሁን ነገር እንደ አምላካችሁ ፈቃድ አድርጉ።

19፤ ስለ አምላክህምቤት አገልግሎት የተሰጠህን ዕቃበኢያሩሳሌምአምላክ ፊት አሳልፈህ ስጥ።

20፤ ከዚህምበላይ ለማውጣት የሚስፈልግህን ለአምላክህ ቤት የሚኖሸውን ነገር ከንጉሡቤተ መዛግብት አውጣ።

21፤ እኔ ምንጉሡአርጤክስስ በወንዝ ማዶ ላሉት በጀሮንዶች ሁሉ ይህን ትእዛዝ ሰጥቻለሁ። የሰማይ አምላክ ሕግ ጸሐፊ ካህኑ ዕዝራ ከእናንተ የሚፈልገውን ሁሉ አዘጋጁለት፤

22፤ እስከ መቶ መክሊት ብርምቢሆን፥ እስከ መቶ የቆሬስ መስፈሪያ ስንዴ፥ እስከ መቶምየ ባዶስ መስፈሪያ የወይን ጠጅ፥ እስከ መቶምየ ባዶስ መስፈሪያ ዘይት ቢሆን፥ ጨውምያለ ልክ ቢሆን ስጡ።

23፤ በንጉሡና በልጆቹ መንግሥት ላይ ቁጣእንዳይሆን፥ የሰማይ አምላክ ያዘዘውሁሉ ለሰማይ አምላክ ቤት በሙሉ ይደረግ።

24፤ ደግሞምበካህናቱና በሌዋውያን በመዘምራኑምበበረኞቹምበናታኒምምበዚህምበእግዚአብሔር ቤት በሚሠሩ አገልጋዮች ላይ ግብርና ቀረጥ መኖንምእንዳይጣል ብለን እናስታውቃችኋለን።

25፤ አንተምዕዝራ፥ በእጅህ እንዳለውእንደ አምላክህ ጥበብ መጠን በወንዝ ማዶ ባሉ ሕዝብ ሁሉ የአምላክህን ሕግ በሚያውቁ ሁሉ ላይ ይፈርዱ ዘንድ ዳኞችንና ፈራጆች አስነሣ፤ የማያውቁትንምአስተምሩአቸው።

26፤ የአምላክህንምሕግ፥ የንጉሣንምሕግ በሚያደርግ ሁሉ ላይ ሞት ወይምስደት ወይምገንዘብን መመረስ ወይምግዞት በፍጥነት ይፈረድበት።

27፤ 28፤ በኢያሩሳሌምያለውን የእግዚአብሔርን ቤት ያሳምር ዘንድእንደዚህ ያለውን ነገር በንጉሡልብ ያኖረ፥ በንጉሡምበአማካሪዎቹምበንጉሡምታያላን አለቆች ሁሉ ፊት ምሕረቱን ወደ እኔ የላከ የአባቶቻችን

አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ። እኔ ምበላዬ ባለችውበአምላኬ በእግዚአብሔር እጅ በረታህ፤ ከእኔ ምጋር እንዲወጡከእስራኤል ዘንድ አለቆችን ሰበሰብሁ።

ምዕራፍ 8።

1፤ በንጉሥበአርጤክስስ መንግሥት ከእኔ ጋር ከባቢሎን የ ወጡየ አባቶች ቤቶች አለቆች እነ ዚህ ናቸው ትወልዳቸውምይህ ነ ው፤

2፤ ከፊንሐስ ልጆች ጌርሶን፥ ከኢታምር ልጆች ዳንኤል፥ ከዳዊት ልጆች ሐጡስ፥ ከሴኬንያ ልጆች፥

3፤ ከፋሮስ ልጆች ዘካርያስ፥ ከእርሱም ጋር መኖ አምሳ ወንዶች በትወልድ ተቈጠሩ።

4፤ ከፋሐት ሞዓብ ልጆች የ ዘራእያ ልጅ ኤሊሆዔናይ፥ ከእርሱም ጋር ሀለት መኖ ወንዶች።

5፤ ከሴኬንያ ልጆች የ የ ሕዚኤል ልጅ፥ ከእርሱም ጋር ሦስት መኖ ወንዶች።

6፤ ከዓዲን ልጆች የ ዮናታን ልጅ ዔቤድ፥ ከእርሱም ጋር አምሳ ወንዶች።

7፤ ከኤላምልጆች የ ጎቶልያ ልጅ የ ሻያ፥ ከእርሱም ጋር ሰባ ወንዶች።

8፤ የ ሰፋጥያስ ልጆች የ ሚኪኤል ልጅ ዝባድያ፥ ከእርሱም ጋር ሰማንያ ወንዶች።

9፤ ከኢያአብ ልጆች የ ይሒኤል ልጅ አብደዩ፥ ከእርሱም ጋር ሀለት መኖ አሥራ ስምንት ወንዶች።

10፤ ከሰሎሚት ልጆች የ ዮሲፍያ ልጅ፥ ከእርሱም ጋር መኖ ስድሳ ወንዶች።

11፤ ከቤባይ ልጆች የ ቤባይ ልጅ ዘካርያስ፥ ከእርሱም ጋር ሀያ ስምንት ወንዶች።

12፤ ከዓዝጋድ ልጆች የ ሃቃጣን ልጅ ዮሐናን፥ ከእርሱም ጋር መኖ አሥር ወንዶች።

13፤ ከኋለኞቹ ከአዶኒቃም ልጆች ስማቸውይህ ነ ው፤ ኤሊፋላት፥ ይዐኤል፥ ሸማያ፥ ከእነ ርሱም ጋር ስድሳ ወንዶች።

14፤ ከበጉዋይ ልጆች ዑታይና ዘቡድ፥ ከእነ ርሱም ጋር ሰባ ወንዶች።

15፤ ወደ አኀዋም ወደሜኤስስ መንዝ ሰበሰብኋቸው፥ በዚያ ምሦስት ቀን ሰፈርን፤ ሕዝቡንና ካህናቱን ስቈጥራቸውበዚያ ከሌዊ ልጆች ማንንምአላገ ኘሁም።

16፤ ወደ አለቆቹም ወደ አልዓዛር፥ ወደ አርኤል፥ ወደ ሸማያ፥ ወደ ኤልናታን፥ ወደ ያሪብ፥ ወደ ኤልናታን፥ ወደ ናታን፥ ወደ ዘካርያስ፥ ወደ ሜሹላም፥ ደግሞም ወደ አዋቂዎቹ ወደ ዮያሪብና ወደ ኤልናታን ላክሁ።

17፤ በካሲፍያ ስፍራ ወደ ነ በረውወደ አለቃውወደ አዶ ላክኋቸው፤ ለአምላካችን ቤት አገ ልጋዮችን ያጣልን ዘንድ በካሲፍያ ስፍራ ለሚኖሩት ለአዶና ለወንድሞቹ ለናታኒ ምየ ሚ ግሩአቸውን በአፋቸውአደረግሁ።

18፤ በላያችንምሚልካምበሆነ ውበአምላካችን እጅ ከእስራኤል ልጅ ከሌዊ ልጅ ከሞሖሊ ልጆች ወገ
የነበረውን አስተዋይ ሰውሰራቢያን፥ ከእርሱምጋር አሥራ ስምንቱን ልጆቹንና ወንድሞቹን አማጠልን።

19፤ ደግሞምሐሸብያን ከእርሱምጋር ከሜራሪ ልጆች ወገ ን የነበረውን የሻያንና ሀያውን ወንድሞቹንና
ልጆቻቸውን።

20፤ ሌዋውያንንምእንዲያገለግሉ ዳዊትና አለቆቹ ከሰጡአቸውና ታኒ ምወስጥ ሀለት መቶ ሀያ ና ታኒ ምአማቱ
እነ ዚህምሁሉ በስምበስማቸውተጠሩ።

21፤ በአምላካችን ፊት ራሳችንን እናዋርድዘንድ፥ ከእርሱምየቀናውን መንገድለእኛና ለልጆቻችን
ለንብረታችንምሁሉ እንለምን ዘንድ በዚያ በአጎዋ ወንዝ አጠገ ብጾምአወጅሁ።

22፤ ንጉሡንም፡ የአምላካችን እጅ በሚሹት ሁሉ ላይ ለመልካምነ ው፤ ኃይሉና ቍጣውግን እርሱን በሚተዉሁሉ
ላይ ነውብለን ተናግረን ነበርና በመንገድ ካለውጠላት ያድኑን ዘንድ ሬፍራና ፈረሰኞች ከንጉሥእለምን ዘንድ
አፍሬ ነበርና።

23፤ ስለዚህምነገር ጾምን፥ ወደ እግዚአብሔርምለመንን፤ እርሱምተለመነን።

24፤ ከካህናቱምአለቆች አሥራ ሀለት ሰዎችን፥ ሰራቢያንና ሐሸቢያን ከእነርሱምጋር አሥር ወንድሞቻቸውን
ለየሁ፤

25፤ ንጉሡና አማካሪዎቹ አለቆቹምበዚያምየተገኙት እስራኤል ሁሉ ያቀረቡትን ለአምላካችን ቤት የቀረበውን
ብሩንና ወርቁን ዕቃውንምመዘኜ ሰጠኋቸው።

26፤ ስድስት መቶ አምሳ መክሊት ብር፥ አንድ መቶምመክሊት የብር ዕቃዎች፥ አንድ መቶምመክሊት ወርቅ፥

27፤ ሀያምባለሺህ ዳሪክ የወርቅ ጽዋዎች፥ ሀለትምእንደ ወርቅ የከበሩ ከጥሩ ከሚያንጸባርቅ ናስ የተሠሩ
ዕቃዎች መዘኜ በእጃቸውሰጠሁ።

28፤ እኔም፡ እናንተ ለእግዚአብሔር ተቀደሳችኋል፥ ዕቃዎቹምቅዱስ ናቸው፤ ብሩና ወርቁምለአባቶቻችን
አምላክ ለእግዚአብሔር በፈቃድ የቀረበ ነው፤

29፤ በካህናትና በሌዋውያን አለቆች በእስራኤልምአባቶች ቤቶች አለቆች ፊት በኢያሩሳሌምበእግዚአብሔር
ቤት ጓዳዎች ወስጥ እስከትመዘኑ ድረስ ተግታችሁ ጠብቁ አልኋቸው።

30፤ ካህናቱና ሌዋውያኑምወደ ኢያሩሳሌምወደ አምላካችን ቤት ይወስዱት ዘንድ ብሩንና ወርቁን ዕቃዎቹንም
በሚገ ተቀበሉ።

31፤ በመጀመሪያወሙወር በአሥራ ሀለተኛውቀን ወደ ኢያሩሳሌምእንሄድ ዘንድ ከአጎዋ ወንዝ ተነ ሣን
የአምላካችንምእጅ በላያችን ነበረ፥ በመንገድምከጠላትና ከሚያሸምቅ ሰውእጅ አዳነ ን።

32፤ ወደ ኢያሩሳሌምደረስን፥ በዚያምሦስት ቀን ተቀመጥን።

33፤ በአራተኛወምቀን ብሩና ወርቁ ዕቃዎቹምበአምላካችን ቤት በካህኑ በኦርዮ ልጅ በሜሞት እጅ ተመዘኑ፤ ከእርሱም ጋር የፊንሐስ ልጅ አልዓዛር ነበረ ከእነርሱም ጋር ሌዋውያን የኢያሱ ልጅ ዮዛባትና የቢንዊ ልጅ ኖዓድያ ነበሩ።

34፤ ሁሉምበቀጥርና በሚዛን ተመዘነ ፤ ሚዛኑምሁሉ በዚያን ጊዜ ተጻፈ።

35፤ ከምርኮምየ ወጡት ምርኮኞች ለእስራኤል አምላክ ለሚቃጠል መሥዋዕት ስለ እስራኤል ሁሉ አሥራ ሁለት ወይፈኖች፥ ዘጠና ስድስትምአውራ በጎች፥ ሰባ ሰባትምጠቦቶች፥ ለኃጢኣት መሥዋዕት አሥራ ሁለት አወራ ፍየሎች አቀረቡ። ይህ ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ነበረ።

36፤ የንጉሡንምትእዛዝ በወንዙ ማዶ ላሉት ለንጉሡሹማምቶችና ገዦች ሰጡ፤ እነርሱምሕዝቡንና የእግዚአብሔርን ቤት አገዙ።

ምዕራፍ 9።

1፤ ይህምከተፈጸመበኋላ አለቆቹ ወደ እኔ ቀርበው። የእስራኤል ሕዝብ ካህናቱምሌዋውያኑምእንደ ከነዓናውያን እንደ ኬጢያውያን እንደ ፈርዛውያን እንደ ኢያቡሳውያን እንደ አሞናውያን እንደ ሞዓባውያን እንደ ግብጻውያንና እንደ አሞራውያን ርኩሰት ያደርጋሉ እንጂ ከምድር አሕዝብ አልተለዩም፤

2፤ ለራሳቸውና ለልጆቻቸውምሴቶች ልጆቻቸውን ወስደዋል፥ የተቀደሰውንምዘር ከምድር አሕዝብ ጋር ደባልቀዋል፤ አስቀድሞምአለቆቹና ሹማምቶቹ በዚህ መተላለፍ መጀመሪያ ሆነ ዋል አሉኝ።

3፤ ይህንምነገር በሰማሁ ጊዜ ልብሴንና መሐናጸፊያዬን ቀደድሁ፥ የራሴንና የጢሜንምጠጕር ነጨሁ፥ ደንግጬም ተቀመጥሁ።

4፤ ስለ ምርኮኞቹምመተላለፍ የእስራኤልን አምላክ ቃል የሚፈሩ ሁሉ ወደ እኔ ተሰበሰቡ፤ እኔምእስከ ሠርክ መሥዋዕት ድረስ ደንግጬተቀመጥሁ።

5፤ በሠርክምመሥዋዕት ጊዜ ልብሴና መሐናጸፊያዬ እንደ ተቀደደ ሆኖ ከመዋረዴተነሣሁ፤ በጉልበቴም ተንበርክኬ ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር እጄን ዘረጋሁ።

6፤ እንዲህምአልሁ። አምላኬ ሆይ፥ ኃጢኣታችን በራሳችን ላይ በዝቶአልና፥ በደላችንምወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ብሎአልና አምላኬ ሆይ፥ ፊቴን ወደ አንተ አነሣ ዘንድ አፍራለሁ፥ እፈራማለሁ።

7፤ ከአባቶቻችን ዘመን ጀምረን እስከ ዛሬ ድረስ እጅግ በድለናል፤ ዛሬምእንደ ሆነ ውስለ ኃጢኣታችን እኛና ንጉሦቻችን ካህናቶቻችንምለሰይፍና ለምርኮ ለብዝበዛና ለእፍረት በምድር ነገሥታት እጅ ተጣልን።

8፤ አሁንምቅሬታ ይተወልን ዘንድ፥ በተቀደሰውምስፍራውችንካርን ይሰጠን ዘንድ፥ አምላካችንምዓይናችንን ያበራ ዘንድ፥ በባርነ ትምሳለን ጥቂት የሕይወት መታደስን ይሰጠን ዘንድለጥቂት ጊዜ ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ሞገስ ተሰጥቶናል።

9፤ ባሪያዎች ነንና፥ አምላካችን ግን በባርነ ታችን አልተወንም፤ የሕይወት መታደስን ይሰጠን ዘንድ፥ የአምላካችንንምቤት እንሠራ ዘንድ፥ የተፈታውንምእንጠግን ዘንድ፥ በይሁዳና በኢያሩሳሌምምቅጥር ይደረግልን ዘንድበፋርስ ነገሥታት ፊት ምሕረቱን ሰጠን።

10፤ 11፤ 12፤ አሁንስ አምላካችን ሆይ። ትወርሱአት ዘንድ የምትገቡባት ምድር በምድር አሕዛብ ርኩሰት ረክሳለች፥ ከዳር እስከ ዳርምድረስ ከርኩሰታቸውከጸያፍ ሥራቸውምተሞልታለች፤ አሁንምትበረቱ ዘንድ፥ የምድሩንምፍሬ ትበሉ ዘንድ፥ ለዘላለምለልጆቻችሁ ታወርሱአት ዘንድ ሴቶች ልጆቻችሁን ለልጆቻቸውአትስጡ፥ ሴቶች ልጆቻቸውንምለልጆቻችሁ አትወስዱ፥ ሰላማቸውንና ደኅንነታቸውንምለዘላለምአትሹ ብለህ በባሪያዎችህ በነቢያት ያዘዝኸውን ትእዛዝ ትተናልና ከዚህ በኋላ ምን እንላለን?

13፤ ስለ ክፉ ሥራችንና ስለ ታላቁ በደላችን ካገኘን ነገር ሁሉ በኋላ፥ አንተ አምላካችን እንደ ኃጢኣታችን ብዛት አልቀሠፍኸንምነገር ግን ቅሬታን ሰጠኸን።

14፤ በውኑ ተመልሰን ትእዛዝህን እናፈርስ ዘንድ፥ ርኩስ ሥራን ከሚሠሩ ከእነዚህምአሕዛብጋር እንገባ ዘንድ ይገባናልን? አንተስ ቅሬታየሌለንና የማመልጥ እስክንሆን ድረስ እንድታጠፋን አትቈጣንምን?

15፤ አቤቱ የእስራኤል አምላክ ሆይ፥ አንተ ጻድቅ ነህ፤ ዛሬምእንደ ሆነ ውእኛ አምልጠን ቀርተናል፤ እነሆ በፊትህ በበደላችን አለን፤ ስለዚህ በፊትህ ሊቆምየማቻል የለም።

ምዕራፍ 10።

1፤ ዕዝራምእያለቀሰና በእግዚአብሔር ቤት ፊት እየ ወደቀ በጸለየና በተናዘዘ ጊዜ ከእስራኤል ዘንድ የወንድና የሴት የሕፃናትምእጅግ ታላቅ ጉባኤ ወደ እርሱ ተሰበሰበ፤ ሕዝቡምእጅግ አለቀሱ።

2፤ ከኤላምልጆች ወገን የነበረምየይሔኤል ልጅ ሴኬንያ ዕዝራን እንዲህ ብሎተናገረው። አምላካችንን በድለናል፤ የምድርን አሕዛብእንግዶች ሴቶችን አግብተናል፤ አሁን ግን ስለዚህ ነገር ገና ለእስራኤል ተስፋ አለ።

3፤ አሁንምእንደ ጌታዬና የአምላካችንን ትእዛዝ እንደሚፈሩት ምክር፥ ሴቶቹን ሁሉ ከእነርሱምየተወለዱትን እንሰድድ ዘንድ ከአምላካችን ጋር ቃል ኪዳን እናድርግ፤ እንደ ሕጉምይደረግ።

4፤ ይህምነገር ለአንተ ይገባልና፥ እኛምከአንተ ጋር ነንና ተነሣ፥ አይዞህ፥ አድርገው።

5፤ ዕዝራምተነሣ፤ አለቆቹንና ካህናቱን ሌዋውያኑንምእስራኤልንምሁሉ እንደዚህ ቃል ያደርጉ ዘንድ አማለ፤ እነርሱምማሉ።

6፤ ዕዝራምከእግዚአብሔር ቤት ፊት ተነሥቶ ወደ ኤልያሴብ ልጅ ወደ ዮሐናን ጓዳ ገባ፤ ስለ ምርኮኞቹም ኃጢኣት ያለቅስ ነበርና ገብቶ እንጀራ አልበላም፥ ውኃምአልጠጣም።

7፤ 8፤ ምርኮኞቹምሁሉ ወደ ኢያሩሳሌምእንዲሰበሰቡ፥ እንደ አለቆቹና እንደ ሽማግሌዎችምምክር በሦስት ቀን ወስጥ ያልመጣሁሉንብረቱ ሁሉ እንዲወረስ፥ እርሱምከምርኮውጉባኤ እንዲለይ በይሁዳና በኢያሩሳሌምላይ አዋጅ ነገሩ።

9፤ ሦስት ቀንምሳያልፍ በዘጠኝኛውወር ከወሩምበሀያኛውቀን የይሁዳና የብንያምሰዎች ሁሉ ወደ ኢያሩሳሌም ተሰበሰቡ። ሕዝቡምሁሉ ስለዚህ ነገርና ስለ ታላቁ ዝናብእየተንቀጠቀጠበእግዚአብሔር ቤት ፊት ባለው አደባባይ ተቀመጡ።

10፤ ካህኑምዕዝራ ተነሥቶ። ተላልፋችኋል፤ የእስራኤልን በደል ታበዙ ዘንድ እንግዶችን ሴቶች አግብታችኋል።

11፤ አሁንምለአባቶቻችሁአምላክ ለእግዚአብሔር ተናዘዙ፥ ደስ የሚሰኘውንምአድርጉ፤ ከምድርምአሕዛብና ከእንግዶች ሴቶች ተለዩ አላቸው።

12፤ ጉባኤውምሁሉ በታላቅ ድምፅ መልሰውእንዲህ አሉ። እንደ ተናገርኸን እናደርግ ዘንድ ይገባናል።

13፤ ነገር ግን የሕዝቡቀጥር ብዙ ነው፥ ጊዜውምየትልቅ ዝናብጊዜ ነው፥ በሜዳምልንቆምአንችልም፤ በዚህም ነገር እጅግ በድለናልና ይህ ሥራ የአንድ ወይምየሁለት ቀን ሥራ አይደለም።

14፤ አለቆቻችንምበጉባኤውሁሉ ፋንታ ይቁሙ፤ ስለዚህምነገር የአምላካችን ጽኑ ቍጣከእኛ ይመለስ ዘንድ እንግዶቹን ሴቶች ያገቡት በከተሞቻችን ያሉት ሁሉ በተቀጠረውጊዜ ይምጡ፥ ከእነርሱምጋር የከተማሁሉ ሽማግሌዎችና ፈራጆች ይምጡ።

15፤ ነገር ግን የአሣሄል ልጅ ዮናታንና የቴቁዋ ልጅ የሕዝያ ይህን ነገር ተቃወመ፤ ሜሹላምና ሌዋዊውም ሳባታይ ረዳአቸው።

16፤ ምርኮኞቹምእንዲህ አደረጉ፤ ካህኑ ዕዝራምየአባቶችምቤቶች አለቆች በየአባቶቻቸውቤቶች ተለዩ፥ ሁሉምበየስማቸውተጻፉ፤ በአሥረኛውምወር በመጀመሪያውቀን ነገሩን ይመረምሩ ዘንድ ተቀመጡ።

17፤ እስከ መጀመሪያውወር እስከ መጀመሪያውቀን ድረስ ሠረተውእንግዶቹን ሴቶች ያገቡትን ሰዎች ሁሉ መርምረውጨረሱ።

18፤ ከካህናቱምወገን ልጆች እንግዶቹን ሴቶች ያገቡሰዎች ተገኙ፤ ከኢዮሴዴቅ ልጅ ከኢያሱ ልጆችና ከወንድሞቹ፥ መዕሤያ፥ አልዓዛር፥ ያሪብ፥ ጎዶልያስ።

19፤ ሚስቶቻቸውን ይፈቱ ዘንድ እጃቸውን ሰጡ፤ ስለ በደላቸውምከመንጋውአንድ አውራ በግ ለበደል መሥዋዕት አቀረቡ።

20፤ ከኢሜር ልጆችም፤ አናኒና ዝባድያ።

21፤ ከካሪምልጆችምመዕሤያ፥ ኤልያስ፥ ሸሞያ፥ ይሑኤል፥ ዖዝያ።

22፤ ከፋስኩር ልጆችም፤ ኤልዮዔናይ፥ መዕሤያ፥ ይስማኤል፥ ናትናኤል፥ ዮዛባት፥ ኤልዓሣ።

23፤ ከሌዋውያንም፤ ዮዛባት፥ ሰሜኢ፥ ቀሊጣስ የሚል ቀልያ፥ ፈታያ፥ ይሁዳ፥ አልዓዛር።

24፤ ከመዘምራንም፤ ኤልያሴብ፤ ከበረኞችም፤ ሰሉም፥ ጣሌም፥ ኡሪ።

25፤ ከእስራኤልምከፋሮስ ልጆች፤ ራምያ፥ ይዝያ፥ መልክያ፥ ሚያሚን፥ አልዓዛር፥ መልክያ፥ በናያስ።

26፤ ከኤላምልጆችም፤ መታንያ፥ ዘካርያስ፥ ይሑኤል፥ አብዲ፥ ይሬሞት፥ ኤልያ።

27፤ ከዛቱዕ ልጆችም፤ ዔሊዮዔናይ፥ አልያሴብ፥ መታንያ፥ ይሬሞት፥ ዛባድ፥ ዓዚዛ።

28፤ ከቤባይ ልጆችም፤ ይሆሐናን፥ ሐናንያ፥ ዘባይ፥ አጥላይ።

29፤ ከባኒ ልጆችም፤ ሜሉላም፡ መሉክ፡ ዓዳያ፡ ያሱብ፡ ሸዓል፡ ራሞት።

30፤ ከፈሐት ሞኣብ ልጆችም፤ ዓድና፡ ክላል፡ በናያስ፡ መዕሤያ፡ መታንያ፡ ባስልኤል፡ ቢንዊ፡ ምናሴ።

31፤ ከካሪም ልጆችም፤ አልዓዛር፡ ይሺያ፡ መልክያ፡

32፤ ሸሞዐ፡ ስምዖን፡ ብንያም፡ መሉክ፡ ሰሚራ።

33፤ ከሐሱም ልጆችም፤ መትናይ፡ መቱታ፡ ዛባድ፡ ኤሊፋላት፡ ይሬሞይ፡ ምናሴ፡ ሰሜኢ።

34፤ ከባኒ ልጆችም፤ መዕዳይ፡ ዓምራም፡

35፤ ኡኤል፡ በናያስ፡ ቤድያ፡ ከልቅያ

36፤ 37፤ ወንያ፡ ሜሬሞት፡ ኤልያሴብ፡ መታንያ፡

38 መትናይ፡ የዕሡ፡ ባኒ፡ ቢንዊ፡ ሰሜኢ፡

39፤ 40፤ ሰሌምያ፡ ናታን፡ ዓዳያ፡ መካነ ደባይ፡

41፤ ሴሴይ፡ ሸራይ፡ ኤዝርኤል፡ ሰሌምያ፡ ሰሚራያ፡ ሰሉም፡ አሜርያ፡ ዮሴፍ።

42፤ 43፤ ከናባው ልጆችም፤ ይዔኤል፡ መቲትያ፡ ዛባድ፡ ዘቢና፡ ያዳይ፡ ኢዮኤል፡ በናያስ።

44፤ እነ ዚህ ሁሉ እንግዶቹን ሚስቶች አግብተውነ በር፤ ከእነ ዚህም ሚስቶች አያሌዎቹ ልጆችን ወልደውነ በር።